ያግኙን
ስልክ፡- 011 515 08 82
ፋክስ፡- 011 552 64 11 የመጽሐፍ ውይይት በወመዘክር
ፖ.ሳ.ቁ፡- 717
ዌብ ሳይት፡- https://www.nala.gov.et
ፌስቡክ፡- Ethiopian National Archives and Library Agency-ወመዘክር
የኦንላይን ድህረ ገጽ፡- www.wemezeker.nala.gov.et
ቴሌግራም፡- የኢትዮጵያ ብሔራዊ ቤተመዛግብትና ቤተመጻሕፍት አገልግሎት
ዩቲዩብ፡- ወመዘክር National Archive and Library of Ethiopia
የጥሪ ማዕከል፡- 888

ከ1936 ዓ.ም ጀምሮ

# የሰነድና መዛግብት አስተዳደር ክፍልን እናስተዋውቆት!!

ሪከርድ አንድ ድርጅት ወይም ተቋም የተቋቋመበትን ዓላማ ለማስፈጸም በሚያደርገው የእለት ተእለት እንቅስቃሴ አስፈላጊ በመሆኑ የሚፈጠር ወይም ተቋሙ ከሌሎች አካላት የተቀበለው እና ጠብቆ የሚያስተዳድረው የተመዘገበ መረጃ ነው፡፡ መዛግብት ደግሞ አገልግሎታቸውን ከጨረሱ ሪከርዶች መካከል ባላቸው የማስረጃ፣ የማጣቀሻ ፋይዳ በታሪካዊ ማስረጃነት ከትውልድ ወደ ትውልድ የሚተላለፍ እና ለጥናትና ምርምር ቀደምት የመረጃ ምንጭ እንዲሆኑ ለቋሚ ጥበቃ ወደ አብያተ መዛግብት የሚተላለፉ ሪከርዶች ወይም ሰነዶች ናቸው፡፡

በአግባቡ የሚተዳደሩና የሚመሩ ሪከርዶች ወይም መዛግብት ለመልካም አስተዳደር እና ለዴሞክራሲያዊ ሥርዓት መዳበር፣ ለተቋማት ስኬት፣ ለሀገር ልማትና ዕድገት፣ ለትምህርትና ዕውቀት መስፋፋት፣ ለብሔራዊ ስሜት ማበብና መዳበር፣ ዋና መሳሪያ መሆናቸው አጠያያቂ አይደለም፡፡ መዛግብት በአግባቡ ተሰባስበው፣ ተደራጅተውና ተጠብቀው አገልግሎት ላይ እንዲውሉ ከተደረገ በአገር ሁለንተናዊ ዕድገት ላይ የማይተካ ሚና ይጫወታሉ፡፡ የተመዘገቡና ጥበቃ የሚደረግላቸው መዛግብቶችን ለማግኘት ደግሞ አብያተ መዛግብት፣ አብያተ መጻሕፍትና ዶክመንቴሽን ማዕከላት ግንባር ቀደሙን ሥፍራ ይዘው ይገኛሉ፡፡

የኢትዮጵያ ብሔራዊ ቤተመዛግብትና ቤተመጻሕፍት ኤጀንሲ ታሪካዊ ፋይዳ ያላቸውን መዛግብት እያሰባሰበ፣ እያደረጀ እና እየተንከባከበ በመጠበቅ ለትውልድ በማስተላለፍና ለጥናትና ምርምርም ግብዓት ሆነው እንዲያገለግሉ በማድረግ ኃላፊነቱን እየተወጣ ያለ በአዋጅ 179/99 የተቋቋመ መንግሥታዊ ተቋም ነው፡፡

በሀገር ደረጃ የሪከርድ ሥራ አመራርና የመዛግብት አስተዳደርን ሥርዓት ለማስያዝ በዚህ አዋጅ ክፍል ሶስት ላይ ብሔራዊ መዛግብት አስተዳደር በሚል አርዕስት በርካታ ፍሬ ጉዳዮች ተካተዋል፡፡ በአዋጁ አንቀጽ 13 ቁጥር 2 ***"ማንኛውም የሪከርድ አመንጪ መሥሪያ ቤት በየዓመቱ መጨረሻ 25 ዓመት የሚሞላቸውን የማይንቀሳቀሱ ሪከርዶችን ወደ ተቋሙ የሪከርድ ማዕከል ያዛውራል"*** በማለት የሪከርድ አመንጪ ተቋማት ግዴታን በግልጽ ይደነግጋል፡፡

ይህን በአዋጅ የተሰጠውን ኃላፊነት ለመወጣት የሰነድና መዛግብት አስተዳደር ዳይሬክቶሬት ተቋቁሟል፡፡ ይህ ክፍል ከተለያዩ መንግስታዊ ተቋማት እና ታዋቂ ግለሰቦች አዋጁ በሚፈቅደው መሠረት የተሰባሰቡ መዛግብቶችን በአካልና በዳታ ቤዝ በማደራጀት፣ በመዛግብት ለመገልገል ለሚመጡ ተገልጋዮች ማፈላለጊያ መረጃዎችን በማዘጋጀትና ወቅታዊ በማድረግ፣ የክምችት ክፍሉን ስብስብ ይዘት የሚያስተዋውቁ ማፈላለጊያ መረጃዎች በማተምና በማሰራጨት በአካል ለሚመጡ ለውጭ ተገልጋዮችና ተመራማሪዎች ቀልጣፋ አገልግሎት እየሰጠ ይገኛል፡፡

ሪከርዶች፣ መዛግብቶችና የጽሁፍ ቅርሶች በአግባቡ ተሰብስበው፣ ተደራጅተውና ተጠብቀው አገልግሎት ላይ ሲውሉ በርካታ ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ችግሮችን በመፍታትና ባህላዊ እሴቶችን በማዳበር የማይተካ ሚና ይጫወታሉ፡፡

ከዚህ አንፃር የተቋማችን የሪከርድና መዛግብት ማሰባሰብ፣ ማደራጃ እና አገልግሎት አሰጣጥ ሥራ ክፍሎች ከተለያዩ መንግስታዊ ተቋማት እና ታዋቂ ግለሰቦች አዋጅ በሚፈቅደው መሠረት መዛግብትና የጽሁፍ ቅርሶችን በማሰባሰብ፣ በማደራጀት፣ ተንከባክቦ በመጠበቅና ለትውልድ በማስተላለፍ ተመራማሪዎች ጥናትና ምርምር እንዲያደርጉበት ምቹ ሁኔታ በመፍጠር ላይ ይገኛሉ፡፡

በመዛግብት ክምችት ክፍል ከተለያዩ መንግስታዊ ተቋማት እና ግለሰቦች የመነጩ መዛግብት ሲኖሩ ይዘታቸውን ስንመለከት የድንበር ስምምነቶች ፣ ከመሬት ስሪት ጋር በተያያዘ የተፈጠሩ መዛግብቶች ፣ ካርታዎች፣ አቤቱታዎች የተለያዩ ውሳኔ ያረፈባቸው መዳጻጽች፣ ካርታዎች፣ ቻርቶች ፣ ከአመንጪ ተቋማቱ ተግባርና ሃላፊነት ጋር በተያያዘ የመነጩ ታሪካዊና የጥናትና ምርምር ፋይዳ ያላቸው መዛግብቶች፣ ፖሊሲዎች፣ የከፍተኛ ኃላፊዎች የስብሰባ ቃለ ጉባኤዎች፣ ጋዜጣዊ መግለጫዎች ፣ንግግሮች ፣ እቅዶች ፣ ጥናቶች ፣ ውሎች ፣አዋጆችና ደንቦች ፣ ትላልቅ ህዝባዊና ሃይማኖታዊ እንቅስቃሴዎች፣ የህዝብ ልምዶችና ፍልስፍናዎች፣ አኗኗር ፣ፍላጎቶችን፣ ከሳንሱር ክፍል ረቂቅ ቀልዶች፣ አባባሎች፣ ግጥሞች፣ ቲያትሮች፣ ተውኔቶች፣ ድራማዎች፣ በእየሩሳልም ገዳም ዙሪያ ስላሉ ክርክሮች ወዘተ ይገኛሉ፡፡

በአጠቃላይ በኢትዮጵያ ቤተመዛግብትና ቤተመጻህፍት አገልግሎት የመዛግብት ክምችት ክፍል ሀገሪቱ ያለፈችባቸውን ፖለቲካዊ፣ ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ ሃይማኖታዊና ባህላዊ እንቅስቃሴዎች በማሳየትና ቋሚ ምስክር በመሆን ያለፈውን፣ የአሁኑንና የመጪውን ትውልድ የሚያስተሳስሩ የዘላለማዊት ኢትዮጵያ ምስል ማመላከቻ መስታዎቶች የሆኑ ቅርሶችን ይዞ ይገኛል፡፡

## የመዛግብት ክምችት ክፍላችን እውነታዎች

- የዛሬው የኢትዮጵያ ቤተመዛግብት እና ቤተመጻሕፍት አገልግሎት መዛግብቶችን ማሰባሰብ የጀመረው ከ1973 ዓ.ም ጀምሮ ነበር፡፡
- ወደ መዛግብት ክምችት ክፍል የገቡት የመጀመሪያዎቹ ሪከርዶችና መዛግብቶች ከአልጋ ወራሽ ግቢ እና ከግቢ ሚኒስቴር ነበር፡፡
- የክምችት ክፍሉ የሚገኙ መዛግብት የሚሸፍኑት ዘመን ከ 1918 እስከ 1998 ድረስ ያለውን ነው፡፡
- በክምችት ክፍሉ በርካታ ስብስብ ያለው ተቋም የቀድሞው የአገር ግዛት ሚንስቴር ነው፡፡
- በክምችት ክፍሉ ውስጥ ከ30 በላይ ተቋማት መዛግብት እና የ6 ግለሰቦች የጽሁፍ ቅርሶች የሚገኙ ሲሆን የግቢ ሚኒስቴር ፣ የአልጋ ወራሽ ግቢ እና የአገር ግዛት መዛግብቶች በሲሪ የተከፈሉ በመሆናቸው አልጋ ወራሽ ዘጠኝ ፣ ግቢ ሚኒስቴር ስምንት ሥራ ክፍሎች፣ አገር ግዛት ደግሞ አስራ አራት ጠቅላይ ግዛቶችና ሶስት ሥራ ክፍሎች የመነጬ መዛግብቶችን በሥራቸው ይዘው ይገኛሉ፡፡
- በመዛግብት ክምችት ክፍሉ ያሉ መዛግብቶች ሼልፍ ርዝመት ከ 3 እስከ 4 ኪሎ ሜትር ይደርሳል፤
- በተቋሙ በዓለም ቅርስነት የተመዘገቡ 12 የጽሁፍ ቅርሶች ይገኛሉ፡፡
- በክምችት ክፍሉ 3000 ፎቶ ግራፎች በላይ ይገኛሉ፡፡

## በመዛግብት ሥራ ክፍል የሚሰጡ አገልግሎቶች

የመዛግብት ንባብ ፣ የፎቶ ኮፒ፣ የዲጂታል ኮፒ እና የጉብኝት አገልግሎት

በመዛግብት ሥራ ክፍል አገልግሎት ለማግኘት ማንነትን የሚገልጽ የታደሰ መታወቂያ ይዞ መቅረብን ይጠይቃል፡፡ እሁድና በህዝባዊ በአላት ቀን አገልግሎት አይሰጥም፡፡

## የአገልግሎት ሰዓት

ከሰኞ እስከ አርብ ጠዋት፡- 2፡30 እስከ 6፡30

ከሰዓት፡- 7፡30 እስከ 11፡30